# የቆዳ ኢንደስትሪ መፃኢ ግዜ ብሩህ ነው

*ከኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት*
*ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት*
*12-24-14*

## የኢትዮጵያ የቆዳ ኢንደስትሪ ታሪካዊ ዳራ

የአንድ ምእተ ዓመት ዕድሜ ያለው የቆዳ ኢንዱስትሪ በአገራችን አንጋፋ ከሚባሉት ኢንዱስትሪዎች ቀዳሚ ነው፡፡ጥንት ለበርካታ አገልግሎቶች ይውል የነበረው ቆዳ በአሁኑ ጊዜ ለአልባሳት (ለጃኬት፣ ለሰደሪያ፣ ለጫማ፣ ለቀበቶ ፣ ለቦርሳ፣ ለጓንት እና ለመሳሰሉት) መስሪያነት እና ለጫማ ብቻ የተገደበ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

አፈንዲ ሙተቂ ፣በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚኖሩት የኦሮሞ፣ የሀረሪ እና የሶማሊ ህዝቦች ቆዳን ለ37 ቁሳቁሶች መስሪያነት ይጠቀሙበት እንደነበር **ኡመተ ፈናን ኡመተ ቀሽቲ ዲሬዳዋ** በተባለው መጽሐፉ ላይ ገልጿል፡፡ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ትልካቸው ከነበሩት መካከል ዝባድ፣ የዝሆን ጥርስ … ቆዳ በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል፡፡

በአገራችን ቆዳ ኢንዱስትሪ ውስጥ ሁነኛ ስም ካላቸው አንዱ የሆኑት ባለሀብት ሐጂ በዳዳ፣ በአንድ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር እንደጠቀሱት፣ የመጀመሪያው ቆዳ ፋብሪካ የተቋቋመው በሐረር ከተማ እ.ኤ.አ 1907 ነው ፡፡ በዚያ ዘመን አንድ አርመናዊ የቆዳ ፋብሪካ ለማቋቋም በወቅቱ የሐረርጌ ገዥ ለነበሩት ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ፣ ፋብሪካውን አቋቁመዋል፡፡ፋብሪካውም የተወሰኑ ዓመታት ከሰራ በኋላ መቆሙን ባለሀብቱ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል ለአገራችን የመጀመሪያ የሆነው ቆዳ ፋብሪካ የአዲስ አበባ ቆዳ ፋብሪካ መሆኑን ሰኔ 1981 ዓ.ም የታተመው፣ የፋብሪካው መጽሔት ያስረዳል፡፡መጽሔቱ እንደሚጠቅሰው ከሆነ ፋብሪካው የተቋቋመው በ1918 በውሃ በሚሰራ ወፍጮ ቤት ውስጥ

ሲሆን የተመሰረተውም ሙሴ እስክንድር እና ሙሴ ሳቫጂያን በተባሉ ሁለት አርመናውያን መካከል በተደረገ የሽርክና ውል ነው፡፡ የምርት መሳሪያውም ቢላዋ ብቻ ነበር፡፡ ፋብሪካው በወቅቱ ተፈላጊ የነበሩትን ዝናር፣ ቀበቶ፣ የአገልግል ሽፋን፣ የኮርቻ ሽፋን፣ የመሳሰሉ የቆዳ ምርቶችን ያመርት የነበረ ሲሆን፣ ለቀለምነት ቅጠላ ቅጠሎችን እንደ ኬሚካል ይጠቀም ነበር፡፡

በሁለቱ ሽርኮች መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ ሙሴ እስክንድር ከሽርክናቸው እንዲወጡ ተደርጎ በምትካቸው ሌሎች አምስት የውጭ አገር ዜጎች ተጨምረው ከ1921-1928 የጋራ ይዞታ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከ1928 በኋላ ግን ሙሉ በሙሉ በሙሴ ሳቫጂያን ይዞታ ስር እንደነበር ይነገራል፡፡

በአነስተኛ የሰው ኃይልና ወጪ ተመስርቶ በመስራት ላይ የነበረው ይህ ፋብሪካ ከዝቅተኛ ደረጃ የቆዳ ማልፋት ስራ፣ ዕድገት በማሳየት እና በማስፋፋት  ቀድሞ አስኮ ጫማ ፋብሪካ አሁን ጥቁር ዐባይ ጫማ ፋብሪካ ተብሎ የሚጠራውን ድርጅት አቋቁሟል፡፡

ይኸው ድርጅት በ1967 ዓ.ም የማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅቶችን የመንግስት ይዞታ ባደረገው አዋጅ ወደ መንግስት ይዞታነት ሲዛወር፣ 150 ቋሚ ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን ካፒታሉም ብር 973,889 ደርሶ ነበር፡፡

የመጀመሪያዎቹን ሁለት የቆዳ ፋብሪካዎችን ተከትሎ የተመሰረቱት የአስኮ ቆዳ ፋብሪካ (አሁን አዲስ አበባ የቆዳ ፋብሪካ )እና የአስኮ ጫማ ፋብሪካ (አሁን ጥቁር አባይ) እና ዳርማር የቆዳ ፋብሪካ (አዋሽ የቆዳ ፋብሪካ - ኢ.ሊ.ኮ) እና ዳርማር የጫማ ፋብሪካ ( አሁን አንበሳ የጫማ ፋብሪካ) ናቸው፡፡

ግሩም አበበ እና ፍሎሪያን ስቻፈር High Hopes and Limited Successes: Experiencing with Industrial Policies in the Leather Industry in Ethiopia በሚል ርዕስ December,2013 በሰሩት የምርምር ጽሁፍ ላይ፣ በዘመኑ የነበሩት የቆዳ ፋብሪካዎች በአብዛኛው ልማዳዊ እና ኋላ ቀር የአመራረት ዘዴን ይጠቀሙ ስለነበር ውጤታማ

እንዳልነበሩ ጠቁመዋል፡፡ በወቅቱ የነበረው መንግስትም የጥሬ ቆዳና ሌጦን ጥራት ለማስጠበቅ እኤአ በ1964 በአዋጅ የቁም ከብት እና የስጋ ቦርድ አቋቁሞ ነበር፡፡ ይህ ቦርድ ዘመናዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓት እንዲዘረጋ ጥረት አድርጓል፡፡ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርትና ግብይት ስርዓት ላይ የሚሰማሩ ተዋንያን እና ደጋፊ አካላት በግብይት እንቅስቃሴ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና እንደጥሬ ምርቶቹ ግብይት በጥራት ላይ ተመስርቶ፣ ለተሻለ ጥራት የተሻለ ክፍያ እንዲፈጸም በማድረግ የውድድር መንፈስ እንዲጎለብት ተሞክሯል ፡፡

ደርግ ስልጣን በያዘ በሦስት ወሩ ታሕሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም የግል ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅቶችን ወደ መንግስት ይዞታነት እንዲዛወሩ ባወጣው አዋጅ ድሬ የቆዳ ፋብሪካ ሲቀር ሌሎች ፋብሪካዎች ተወረሱ፡፡የኢኮኖሚ ስርዓቱም ወደ ዕዝ ኢኮኖሚ እንዲለወጥ በማድረጉ፣ በንጉሰ ነገስቱ ዘመን የሚያበረታታ ጅምር የነበረው የቆዳ ኢንዱስትሪ ከነበረበት ደረጃ አሽቆለቆለ፡፡

## የቆዳ ኢንዱስትሪ ባለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት

በሁለት የጫማ ፋብሪካዎች የተጀመረው የጫማ ኢንዱስትሪ እስከ 1983 ድረስ በፋብሪካዎች ቁጥር ዕድገት ሳያሳይ ቆይቷል፡፡የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ ነጻ የገበያ ስርዓት በመፈጠሩ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው እድገት በማሳየት ዓለም አቀፍ አድናቆትና እና እውቅናን አግኝቷል፡፡

መንግስት ለቆዳ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ፣ ዘርፉ በምርት ጥራትና ብዛት በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለሀገሪቱ የሚያስገኘው ጥቅም ከፍ እንዲል ለዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀብት የሚያፈራ፣ የምክርና የቴክኒክ አገልግሎቶችን የሚሰጥ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/91 በ1991 ዓ.ም የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንስቲትዩትን አቋቁሟል፡፡

ይህ ኢንስቲትዩት፣ ለቆዳው ኢንዱስትሪ ጥራትና ብቃት ያለው ድጋፍ ይሠጥ ዘንድ ቀደም ሲል የወጣውን ደንብ ማሻሻል አስፈልጓል፡፡ ከዚህም አንጻር የቆዳ እንዱስትሪዎች ልማትንና ሽግግርን ማፋጠን እና ፈጣን ልማት ማስመዝገብ የሚችሉ ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪዎችን ማብቃትን፣ ዓላማ ያደረገ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/02 በ2002 ዓም እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

ስያሜው ተሻሽሎ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተባለ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ በአደረጃጀቱና በሚሰጠው አገልግሎት በመስኩ ከአፍሪካ ቀዳሚ ተቋም በመሆን ለበርካታ የአፍሪካ እና የእስያ አገራት ተመክሮውን በማካፈል ላይ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ያለቀላቸው የቆዳ ምርቶችን የሚያመርቱ 31 የቆዳ ፋብሪካዎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ፋብሪካዎች በዓመት 500 ሚሊዮን እስኩዌር ፊት ያለቀለት ቆዳ የማምረት አቅም አላቸው፡፡

በዓመት እስከ 15 ሚሊዮን የሚደርሱ ጥንድ ጫማዎችን የማምረት አቅም ያላቸው 21 መካከለኛ እና ከፍተኛ የቆዳ ጫማ ፋብሪካዎች ተቋቁመው በማምረት ላይ የሚገኙ ሲሆን 4ቱ በፕሮጀክት ደረጃ ላያ ያሉ ናቸው፡፡በተጨማሪ 15 የቆዳ አልባሳትና የቆዳ ዕቃዎችን፣ እንዲሁም 3 የእጅ ጓንቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ተቋቁመው በማምረት ላይ ይገኛሉ፡፡

በንዑስ ዘርፉ ትኩረት ከተሰጣቸው አንዱ በማይክሮ እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ለሚደራጁ ዜጎች አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ሲሆን፣ ከ2 ሺ ብር እስከ 220 ሺ ብር መነሻ ካፒታል ያላቸው፣ እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡በዚህም መሰረት በመላው አገሪቱ 368 ማይክሮ እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ቡድኖች ተደራጅተው የቆዳ ውጤቶችን በማምረት ላይ ይገኛሉ፡፡

## ከእንስሳት አገልግሎት የማይሰጠው ድምጻቸው ብቻ ነው፡፡

እንስሳት ዘርፈ ብዙ ጥቅም አላቸው፡፡ በቁማቸው ወተትና እና ጸጉራቸው ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሁም ለትራንስፖርትና ለእርሻ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡በተለይ ለአርሶ አደሩ ባለውለታ ናቸው፡፡ አርሶ አደሩ በስነ ቃል በሬን ፣

*"በሬ ካላንተማ አያ ካላንተማ*
*ዓይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሰማ*
*በሬ ያለህ ማነው ስምህን አሳንሶ*
*መንግስተ ሰማያት ሳይልህ ጨርሶ"*

እያለ ያወድሰዋል፡፡ ከእርድ በኋላም ስጋቸው ለምግብነትና ለመድሃኒትነት፤ ቆዳቸው ለአልባሳት፣ ለጫማ፣ለቦርሳ እና ለሌሎች መገልገያነት ይውላል፡፡የሚሰጧቸው ጥቅሞች ተዘርዝሮ አያልቅም፡፡

የኢትዮጵያ የቆዳ ውጤቶች ምርት በዓለም ገበያ ውስጥ የማይናቅ ሚና ያለው ሲሆን፣ ከሃገር ውስጥ ፍጆታ በተጨማሪ፣ ለዓለም ገበያዎቸ ይቀርባል። ወደውጭ የሚላከው የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ምርት መጠን በብዛትመ ሆነ በጥራት በማደግ ላይ ይገኛል።

አገሪቱ ባለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት  አንድ ቢሊዮን አራት መቶ አርባ አራት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ አግኝታለች፡፡በ1984 በጀት ዓመት ከኤክስፖርት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ 28.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት  132.95 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ ባለፈው ዓመት የተገኘው የኤክስፖርት ገቢም ካለቀለት ቆዳ፣ ከጫማ፣ ከቆዳ ጓንት፣ ከቀበቶ፣ ከተለያዩ የቦርሳ አይነቶች፣ ከቆዳ አልባሳት (ጃኬት፣ ኮት፣ ሱሪ፣ የሶፋና ሎሎች ማላበሻ ወይም መሸፈኛዎች እንዲሁም ከሌሎች የቆዳ ምርቶች ነው።

የኢትዮጵያ የቆዳ ጫማዎች እና የቆዳ ምርቶች ከንፁህ ቆዳ የተሰሩና በዋጋመ ሆነ በጥራት ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነተ መስፈርትን ያሟሉ በመሆናቸው በዓለም ገበያ ተፈላጊነታቸው በመጨመር ላይ ይገኛል። ጣልያን፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ቻይና እና ጃፓን እንዲሁመ የሩቅና መካከለኛምስራቅ ሃገራት እና የአፍሪካ ሃገራት የኢትዮጵያ ቆዳና ሌጦ ምረቶቸ መዳረሻ ናቸው።

ከዚህ አንፃር በ2006 በጀት ዓመት ለተገኘው አጠቃላይ የኤክስፖርት ገቢ (132.95 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር )፣ ካለቀለት ቆዳ 73.48 በመቶ፣ከጫማ 22.97 በመቶ እና ከቆዳ ጓንትና ከሌሎች የቆዳ ውጤቶች 3.55 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡በ2005 በጀት ዓመት በተመሳሳይ ምርቶች  የተገኘው 123.44 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን፣ የ2006 በጀት ዓመት ገቢ ከ2005 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር ፣ የ9.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጭማሪ፣ በመቶኛ ደግሞ የ7.7 ዕድገት አሳይቷል፡፡

በ2006 በጀት ዓመት ከፍተኛ የእሴት ጭማሪ ያላቸው ምርቶች (የጫማ፣ የቆዳ ጓንትና የቆዳ አልባሳት ዕቃዎች) ከጠቅላላው ኤክስፖርት 26.52 በመቶ ድርሻን ይዘዋል፡፡ ይህም ከ2005 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ57.24 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በ2006 በጀት ዓመት ከጫማ ምርት ኤክስፖርት የተገኘው 30.54 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ሲሆን ይህም ከ2005 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ11.35 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጭማሪ፣ 59.13 በመቶ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡

በዚሁ ዓመት ቆዳ ጓንትን ጨምሮ ከሌሎች ከፍተኛ የእሴት ጭማሪን ካረጋገጡ የቆዳ ውጤቶች ኤክስፖርት፣ 4.71 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህም በ2005 በጀት ዓመት ተገኝቶ ከነበረው 3.23 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የወጪ ንግድ ገቢ ጋር ሲነጻጸር ወደ 46 በመቶ ዕድገት እንደተገኘ ያመለክታል፡፡

ንኡስ ዘርፉ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ላይ ይገኛል ፡፡ በቆዳ ፋብሪካዎች 8,346፣ በጫማ ፋብሪካዎች  5,602፣ በቆዳ ጓንት 659 እና በቆዳ ዕቃዎችና አልባሳት 1,037 በጠቅላላው 15,644 ዜጎች በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂዎች ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት ማስመዝገብ እንዲችሉ፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት  የገበያና የግብዓት ትስስር በመፍጠር ጉልህ ድርሻ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም በቆዳና ቆዳ ውጤቶች የተደራጁ 1289 አባላት ያሉዋቸው፣ 448 ኢንተርፕራይዞች እና በጫማ ስራ 171 አባላት ያሉዋቸው 93 ኢንተርፕራይዞች፣ በአነስተኛ  እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በመደራጀት ከቆዳ ፋብሪካዎች እና ከጫማ ፋብሪካዎች ጋር የገበያና የግብዓት ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው፡፡

በአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የተደራጁ ማኅበራት ከጫማና ከቆዳ ፋብሪካዎች ጋር የገበያ፣ የሥራና የግብዓት ትስስር ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በተፈጠረው የሥራ ትስስርም ፣ ፋብሪካዎች በኢንተርፕራይዝ ማኅበራቱ ደረጃ የሚሰሩ ሥራዎችን(የጫማ Upper ስፌት፣ ሞካሲል ስፌት… ) ማኅበራቱ እንዲሰሩ በማድረግ የገቢ አቅማቸውን በማጎልበት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ኢንተርፕራይዝ ማኅበራት  ውስጥ አንዱ ለቆዳ ፋብሪካዎች ግብዓት አቅራቢ ሁኗል፡፡

በአገር ውስጥ የሚገኙ የጫማ ፋብሪካዎች ያለቀለት ቆዳ፣ ከቆዳ ፋብሪካ እንዲያገኙ ከመደረጉም በላይ ኢንስቲትዩቱ በቆዳ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ፋብሪካዎች ከአፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ ገበያ ጋር ትስስር መፍጠር የሚያስችል የገበያ ስትራቴጂ (Market Strategy) ጥናት በከፍተኛ ባለሙያዎች በማስጠናት ላይ ይገኛል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት የተሰማሩ ፋብሪካዎች ወደ ውጭ የሚልኳቸው ምርቶች እና ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡዋቸው ግባቶች ደረጃቸውንና ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ የላቦራቶሪ ፍተሻ በማድረግ ሰርተፊኬት ይሰጣል፡፡  ከደንበኞችም ሆነ ከአቅርቦት አንጻር ችግሮች ሲያጋጥማቸው  ኢንስቲትዩቱ ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ላይ ነው፡፡

## አቅም ግንባታ

አገሪቱ የተያያዘችውን ፈጣን እድገት ለማስቀጠል የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ይህን ንኡስ ዘርፍ እንዲደግፍ የተቋቋመው የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በቅድሚያ የራሱን አቅም እንዲገነባ በመንግስት አቅጣጫ ተሰጥቶታል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ከሚያከናውቸው ተግባራት መካከል በራሱና በሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አማካይነት ለቆዳ ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል በማልማት፣ የዓለም ገበያ በሚፈልገው ደረጃ ማምረት የሚችል ባለሙያ ለማብቃት የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ማካሔድ ነው፡፡

በዚህ መሰረትም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ሕንድ ከሚገኙት ስመጥር ሁለት ኢንስቲትዩቶች CSIR-CLRI እና FDDI ጋር ራሱን በማቆራኘት ባለፉት ሦስት ዓመታት ሁሉን አቀፍ ከፍተኛ የአቅም ግንባታ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ በርካታ የውስጥ አቅም ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን በጥቂት ዓመታት ውስጥ በድጋፍ አሰጣጡና በተቋማዊ አቅሙ ደረጃውን የጠበቀና የቆዳ ኢንዱስትሪን ትራንስፎርም ሊያደርግ የሚችል ተቋምን መፍጠር ነው፡፡ የኢንስቲትዩቱን አቅም ከማሳደግ አንጻር በአጫጭር የሥልጠና ፕሮግራም 87፣ በሁለተኛ ዲግሪ የሥልጠና ፕሮግራም 32 እንዲሁም በሦስተኛ ዲግሪ ፕሮግራም 6 የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

ከፕሮግራሙ የሚጠበቀውን አጠቃላይ ውጤት እውን በማድረጉ ሂደትም በዕቅድ ተይዘው የተከናወኑ ተግባራት በአራት አቢይ ሥራዎች ይጠቃለላሉ፡፡
የኢንስቲትዩቱን የማኔጅመንት አደረጃጀት እንዲሁም የአሠራር ሥርዓት ማሻሻልና ውጤታማ ማድረግ፣ የኢንስቲትዩቱን ባለሙያዎች እንደ መነሻ በመጠቀም የቆዳ ሳይንስን፣ የምርምርና ስርፀት ሂደትንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በቆዳ ንዑስ ዘርፍ ማስፋፋት ፣በንዑስ ዘርፉ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ምርትና ምርታማነት ማጠናከርና ማስፋፋት እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና በጥራቱም አስተማማኝ የሆነ ምርት በማልማት እና በማሸጋገር ንዑስ ዘርፉን በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ማድረግ ነው፡፡

ባለፉት ሦስት ዓመታት የተካሔደው የቁርኝት ፕሮግራም ኢንስቲትዩቱ የውስጥ አቅሙን እንዲገነባ ጉልህ ድርሻ አበርክቷል፡፡ ለቆዳ፣ ለጫማና ለጓንት ፋብሪካዎችም የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ እነዚህ የአቅም ግንባታ ስራዎችም ለቆዳ ኢንዱስትሪ ስኬት ያበረከቱት ድጋፍ ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህን ስኬቶች ለመዘከር እና አጠናክሮ ለማስቀጠል ፤ **"የቁርኝት ፕሮጀክት ውጤቶችና መጻኢ እድሎች "** በሚል መሪ ቃል መስከረም 6 ቀን 2007 ዓ.ም ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ የሆኑ አምባሳደሮች፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በታላቅ ድምቀት ተከብሯል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ ጋር በቁርኝት ፕሮግራም በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን የቆዳ ቴክኖሎጂ ትምህርት ክፍል እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በ2005 ዓ.ም በቆዳ ቴክኖሎጂ 14 ተማሪዎች በ2006 ዓ.ም ደግሞ 14 ተማሪዎች በቢ ኤስ ሲ ዲግሪ ተመርቀዋል፡፡

እነዚህ ሰልጣኞችና ተመራቂዎች በቆዳ ኢንዱስትሪ የስራ መስኮች በቆዳ ኢንዱስትሪ ውስጥ በመቀጠር የበኩላቸውን ድርሻ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡
በ2006 በጀት ዓመት ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር በጫማና በቆዳ እቃዎች ቴክኖሎጂ ትምህርት በዲግሪ ፕሮግራም መጀመር የሚያስችል፣ የቅድመ ዝግጅት ስራና የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ተጠናቆ በዚህ በጀት ዓመት የተጀመረ ሲሆን፣ 17 ወንድ እና 3 ሴት በድምሩ 20 ተማሪዎች በመማር ላይ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በቆዳ አመራረት ኢንዱስትሪ ትምህርት መርሐግብር 49 ወንድና 10 ሴቶች በድምሩ 59 ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡

ኢንስቲትዩቱ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በመደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መርሐ ግብር 896 ወንድ 641 ሴት በድምሩ 1537 ተማሪዎችን በቆዳ አመራረት በጫማ አመራረት እና በቆዳ አልባሳትና እቃዎች አመራረት የሙያ መስኮች በዲፕሎማና በሰርተፊኬት አሰልጥኖ አስመርቋል ፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ምርትና ምርታማነት የላቀ ደረጃ ላይ መድረስ የሚችለው በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት ሲቻል ነው ፡፡ ከዚህም አንጻር ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ስልጠናዎች ተደራሽነት ለማረጋገጥ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ከተስፋፋባቸው ክልሎች ጋር በመስራት ላይ ነው፡፡ ባለፈው ክረምት ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ፣ ከአዲስ አበባ እና ከድሬደዋ ከተማ መስተዳድሮች ቴክኒክና ሙያ ትምህትና ስልጠና ኮሌጆችና ተቋማት ለተወጣጡ 82 ወንድ 40 ሴት በድምሩ 122 አሰልጣኞች በጫማ አመራረት እና በቆዳ አልባሳትና እቃዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ ኢንስቲትዩቱ ለቴክኒክና ሙያ ትምህትና ስልጠና ተቋማት ባለሙያዎች የሚሰጠው ስልጠና የቆዳ ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን በብዛትና በጥራት በማሳደግ በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡
በተግባር ተኮር አጫጭር ስልጠናም ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች በቆዳ አመራረት፣ በጫማ እና በቆዳ አልባሳትና እቃዎች አመራረት በ2006 በጀት ዓመት 375 ባለሙያዎች ሠልጥነው ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ኢንስቲትቱዩቱ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በመደበኛ መርሐ ግብር ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ 581 ወንድና 840 ሴት በድምሩ 1403 ተማሪዎችን በቆዳ አመራረት፣ በጫማ አመራረት እና በቆዳ አልባሳትና እቃዎች አመራረት የሙያ መስኮች በዲፕሎማና በሰርተፊኬት አሰልጥኖ አስመርቋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በቆዳ ውጤቶች በደረጃ I እና II ሰልጣኞችን በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ፡፡ከሚሰጧቸው የትምህርና ሥልጠና ፕሮግራሞች በተጨማሪ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት በአዲስ አበባ በሚገኙ 6 የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ በኦሮሚያ 9 ተቋማት እንዲሁም በትግራይ፣ በአማራና በደቡብ ክልሎች በሚገኙ የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በደረጃ I እና II ፕሮግራም ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በክረምት ስልጠና ፕሮግራምም፣በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚያስተምሩ መምህራን እና ባለሙያዎች የክረምት ትምህርት የተለያዩ ደረጃዎች በማሰልጠን፣ በተላኩበት ተቋም ተመልሰው እንዲያሰለጥኑ እየተደረገ ነው፡፡

በተግባር ተኮር አጫጭር ስልጠናም ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎች በቆዳ አመራረት፣ በጫማ አመራረት እና በቆዳ አልባሳትና እቃዎች አመራረት በ2006 በጀት ዓመት 133 ወንድና 32 ሴት በድምሩ 165 ባለሙያዎች የስልጠናው ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን 31 የቆዳ ፋብሪካዎች የሚገኙ ሲሆን በዓመት 194 ሚሊዮን ካሬ ጫማ (43 ሚሊዮን ሌጦ) የማጠናቀቅ አቅም ላይ ቢደርሱም፣ የሚያመርቱት በአገሪቱ ሊመረት ከሚችለው የጥሬ ሌጦ መጠን 58 በመቶ አቅማቸውን ብቻ ነው፡፡

በ2006 በጀት ዓመት 17 ሚሊዮን ጥሬ ሌጦ ለፋብሪካዎች ቢደርስም አገራችን ካላት የእንስሳት ሀብት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በፋብሪካዎች የሚታየውን የጥሬ ሌጦ አቅርቦት ችግር በማቃለል የምርትና የኤክስፖርት ገቢን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ ፋብሪካዎች ጥሬ ሌጦ ከውጭ እንዲያስገቡ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በያዝነው በጀት ዓመትም የጥሬ ግብዓቱን አቅርቦትና የጥራት መጓደል ለማስወገድ እንዲቻል በመንግስት ቀጥተኛ ድጋፍ ከውጭ በጥሬ፣ በፒክል፣ በዌትብሉና በክረስት ደረጃ የተዘጋጁ ምርቶች ወደ አገር ውስጥ ገበያ እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

## የቆዳ ኢንደስትሪ ልማት አንፀባራቂ ተስፋ

ሃገራችን በእንስሳት ሃብት ይዞታዋ ከአፈሪካ ቀዳሚ ስተሆን ከዓለም ደገሞ አስረኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በዚህ ሃብቷ በየአመቱ 2.7 ሚሊየን የከብት ቆዳ፣ 8.1 ሚሊየነ የበግ ሌጦ እና 7.5 የፍየል ሌጦ ታመርታለች። ይህ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ዋጋ በከፊል ከተዘጋጁ ቆዳዎች ጋር ሲነፃፀር ዋጋወ እስከ 60 በመቶ ያህል ብቻ ነው።

ይህም በእንስሳት ሀብትዋ በሙሉ እየተጠቀመች አለመሆንዋን ያመለክታል፡፡አገሪቱ በዚህ ሀብት ተጠቃሚ እንደትሆን መንግስት የተለያዩ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ነድፎ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ሲሆን የቆዳና ቆዳ ውጤት ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጂ ልማትንና ሽግግርን በማፋጠን በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በቆዳ ቴክኖሎጂ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጀምሮ እስከ ቢኤስ ሲ ዲግሪ ደረጃ ባሉ ፕሮግራሞች በአገር ውስጥ ትምህርት እየተሰጠ ከመሆኑም በተጨማሪ በውጭ አገር በማስተርስና በዶክትሬት ዲግሪ ፕሮግራም፣ ባለሙያዎችን በማሰልጠን የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማስፋፋት ላይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ኢንቨስትመንትን የመሳብ ስራዎቸ እየተከናወኑ ሲሆን፣ በመሰኩ ለሚሰማሩ ኢነቨሰተሮች፤ ስለምርት፣ ስለገበያ፣ ስለቴክኖሎጂ የምክርና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል። ግዙፍ የሆኑ ኢነቨስትመንቶች ወደ ንኡስ ዘረፉ እየመጡ ነው።
በንኡስ ዘርፉ የተሰማሩ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች አቅማቸው እያደገ ነው፡፡ኮልባ ቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ኃላፊነቱ የተ.የጋራ ማኀበር እና የሞጆ ዘመናዊ ቄራ ፋብሪካ፣ ድሬ ኢንደስትሪስ፣ ሼባ የቆዳ ኢንዱስትሪ፣ ፒኮክ እና ራምሴ የጫማ ፋብሪካዎች በአገራችን ቆዳ ኢንዱስትሪ ውስጥ ሁነኛ ስም አላቸው፡፡

የቻይናው ሁዋጂያን (Huajian)፣ ኒው ዊንግ እና የታይዋኑ ጆርጅ ሹ የጫማ ፋብሪካዎች እንዲሁም የእንግሊዙ ፒታርድስ እና የጀርመኑ  ኦቶክላሰር የቆዳ ጓንት ኩባንያዎች በአገራችን ተጠቃሽ የሆኑ በቆዳ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ናቸው፡፡
ሁዋጂያን (Huajian) ዓለም አቀፍ የጫማ ኩባንያ በኢትዮጵያ የቆዳ ኢንደስትሪ ውስጥ የሁለት ቢሊየን ዶላር ኢነቨስትመንት ለማፍሰስና አንድ መቶ ሺህ ዜጎችን የስራ እድል ተጠቃሚ የሚያሰርግ፣ የኢንደስትሪ ዞን በመገንባት ምርቱን በብዛትና በጥራት ለመጨመር እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኙ እሴቶች የተጨመረባቸውን ምርቶች ማምረት በመጀመሩ ፈጣን ለውጥ በመመዝገብ ላይ ነው፡፡ በዚህም በንዑስ ዘርፉ የሚሳተፉ ባለሀብቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ እና የኤክስፖርት ገቢም በየዓመቱ እድገት ማሳየቱ እንዲሁም የኤክስፖርት ምርትና ተያያዥ የቴክኖሎጂ አቅም ማደጉ፣ መንግስት የወሰዳቸው የፖሊሲ ማሻሻያዎች ወቅታዊና ትክክለኛ እንደሆኑ ያመለክታል፡፡
“ኢንስቲትዩቱን ውጤታማ ተቋም በማድረግ በ2015 የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ በዓለም አቀፍ ያለውን የገበያ ድርሻ በአሥር እጥፍ አድጎ ማየት” የሚል ራእይ ይዞ የተነሳው የቆዳ ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ራዕዩን ለማሳካት የሚያከናውቸው ዘርፈ ብዙ ሥራዎች

ስኬታማ እንደሚያደርጉት ይታመናል፡፡ ስለሆነም ያለው ነባራዊ ሁኔታ የቆዳ ኢንደስትሪ ልማት አንፀባራቂ ተስፋ ያለወ መሆኑን የተገኙ ስኬቶች አመላካች በመሆናቸው መጭው ጊዜ ለቆዳ ኢንዱስትሪ ብሩህ ነው፡፡

<u>የ2005 እና የ2006 በጀት ዓመታት የቆዳና የቆዳ ውጤቶች የኤክስፖርት አፈጻጸም ንጽጽር</u>

| ተቁ | የምርቱ ዓይነት | የ2005 በጀት ዓመት አፈጻጸም | የ2006 በጀት ዓመት አፈጻጸም | እድገት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያለቀለት ቆዳ | 101,020.48 | 97,692.37 | (3.29) |
| 2 | ጫማ | 19,193.92 | 30,543.73 | 59.13 |
| 3 | የቆዳ ጓንት | 3,077.2 | 4,315.63 | 40.25 |
| 4 | የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች | 150.52 | 396.23 | 163.25 |
| | **ድምር** | **123,442.12** | **132,947.96** | **7.7** |

| በጀት ዓመት | ቆዳ | የቆዳ ጫማ | የቆዳ ጓንት | የቆዳ ዕቃዎችና አልባሳት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| 2002 | 12,878.00 | 5,737.00 | - | 138.00 | **18,753.00** |
| 2003 | 95,475.59 | 8,642.08 | - | 213.72 | **104,331.39** |
| 2004 | 100,154.33 | 10,162.95 | 1,561.05 | 182.25 | **112,060.58** |
| 2005 | 101,020.48 | 19,193.00 | 3,077.20 | 150.52 | **123,441.20** |
| 2006 | 97,692.36 | 30,543.73 | 3,568.84 | 396.23 | **132,201.16** |
| ድምር | **407,220.76** | **74,278.76** | **8,207.09** | **1080.72** | **490,787.33** |